# መልዕክቶቻችን



## ለመላው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን ሰባት

የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት እንኳን ለአዲሱ ዓመት ዋዜማ አደረሳችሁ እያለ ዘመኑ የሠላምና የጤና፣ የሥራና የውጤት፣ የደስታና የብልፅግና እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቱን ይገልፃል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን የሙከራ ትግበራ የጀመረባቸውን የክረምት ወራት እያጠናቀቀ ወደ ፀደይ በመሸጋገር ላይ ይገኛል፡፡ የአዲሱ ዓመት መባቻ ወር ደግሞ ሙከራው ዘላቂ መሠረት በሚጥል አጀማመር መገባደዱ አየተረጋገጠ ወደሙሉ ትግበራ የመግባት ጉዞ የሚጀመርበት በመሆኑ ለበለጠ ሥራ የምንዘጋጅበት የለውጥ ጊዜ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በአዲሱ ዓመት ዋዜማ ላይ ሆነን መጪውን የሥራ ዘመን አሻግረን ስንመለከት የኢትዮጵያን ሕዳሴ የማብሰር አገራዊ ድርሻችንን ለመወጣት እንደተቋም ለሕዝብና ለመንግሥት የገባነው ቃል ኪዳን በተግባር የሚገለጽበትና በውጤት የሚለካበት የፅናትና የቁርጠኝነት ጊዜ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህ አኳያ የወሩ አብይ መልዕክቶች በሚከተለው አኳኋን የተላለፉ ሲሆን፤ የእያንዳንዳችንና የሁላችንም የዘወትር ተግባር ምላሻቸው ይሁን እንላለን፡፡

- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተቋቋመለትን ራዕይና ተልዕኮ ጠንቅቆ ማወቅና ለተግባራዊነቱም በተሠማራንበት የሥራ ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት፣
- ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት በመስጠት ጥያቄው ምላሽ ማግኘቱንና ፍላጎቱ መርካቱን ማረጋገጥ፣
- ሁሌም ለለውጥ ዝግጁ መሆንና ሥራዎችን በከፍተኛ ተነሣሽነት ለመፈጸም ዝግጁ መሆን፣
- የሥራ ጊዜን ለመንግሥት ሥራ ብቻ ማዋል፡ በዕቅድ መመራትና ሥራዎችን በታታሪነት በመሥራት ድርሻን መወጣት
- የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ተገልጋዮች በቅንነትና በታማኝነት በማገልገል መልካም ሥነ ምግባር ማሳየትና የተቋሙን መልካም ገፅታ መገንባት፣

**መልካም የሥራ ዘመን!!**

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

# የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሙከራ ትግበራ መጀመሩን ምክንያት በማድረግ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ

የፌደራል ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲያካሂድ የቆየውን የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በማጠናቀቅ የሙከራ ትግበራ መጀመሩን አስመልክቶ ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በመ/ቤቱ የስብሰባ አዳራሽ ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል፡፡ ክቡር አቶ ሐሰን አብደላ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ጋዜጣዊ መግለጫውን በሰጡበት ወቅት ከፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት አንዱ የሆነው የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንዲችል ላለፉት ሁለት ዓመታት የመሠረታዊ አሠራር ለውጥ (BPR) ጥናት ሲያካሄድ መቆየቱን አስረድተዋል፡፡

ጥናቱ በሀገር ውስጥ መልካም የአሠራር ለውጥ ተሞክሮ እያስመዘገቡ የመጡ መ/ቤቶችን ልምድ እንዲያካትት መደረጉንና በአፍሪካና በኤስያ ሀገራት የመ/ቤቱ አምሳያ ከሆኑ ተቋማት ዘመናዊ አሠራር የተገኘውም ልምድ መወሰዱን ሚኒስትሩ ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም በጥናቱ መሠረት ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያበቃ የመነሻ ዝግጅት ተደርጐ ከሐምሌ 2001 ዓ.ም. አንስቶ የሙከራ ትግበራ መጀመሩን ተናግረው ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያን ህዳሴ ለማብሰር የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ አስረድተዋል፡፡



*ክቡር አቶ ሐሰን አብደላ*

ጋዜጣዊ መግለጫውን የተለያዩ የሚዲያ አካላት የተከታተሉ ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለድርሻና አጋር አካላት ማለትም የኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን፣የኢትዮጵያ አረጋውያንና ጡረተኞች ብሔራዊ ማህበር፣ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች፣ የተለያዩ የመንግስት ተቋማት የሥራ ሃላፊዎችና የዓለም ሥራ ድርጅት ተሳትፈዋል፡፡



*የጋዜጣዊ መግለጫው ተሳታፊዎች በከፊል*

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

# ለምኖ አዳሪዎች ወደ ትውልድ ቀያቸው ተመልሰው የሚያለሙ ከሆነ የመንግስት ትብብርና ድጋፍ እንደማይለያቸው ተገለፀ

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ማኒስቴር ከኤልሻዳይ ሪልፍ ኤንድ ዲቨሎፕመንት አሶሴሽን ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር ከልመና በመላቀቅ ወደ ልማት ለመግባት ከተዘጋጁ ወገኖች ጋር **ነሐሴ** 6 **ቀን** 2001 **ዓ.ም**. በዳግማዊ ምኒሊክ መሰናዶ ት/ቤት አዳራሽ ውይይት አካሄደ፡፡

አቶ ***ረመዳን አሽናፊ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ*** ውይይቱን በከፈቱበት ወቅት ልመና ችግርን ከማባባስ በስተቀር ከችግር መውጫ መንገድ እንዳልሆነ አስገንዝበው የአቅማቸውን ያህል እየሠሩ ድህነትን ማሸነፍ የሚችሉ ዜጎች ልመና ላይ በመሠማራታቸው ወገን ሕፍረት እንደሚሰማው  ገልጸዋል፡፡



***ክቡር አቶ ረመዳን አሸናፊ***

ልማትን ለማፋጠንና ሕዝብን ከድህነት ኑሮ ለማውጣት ከልማት ኃይሎች ጋር በቁርጠኝነት እየሠራና የላቀ ውጤት እያስመዘገበ የሚገኘው የኢፌድሪ መንግስት ከሕዝቡ ጋር በመተባበር የአገር አቅም የፈቀደውን ያህል ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ አያይዘውም ለመከራ ኑሮ የዳረጋችውን ልመና አውግዘው ለልማት መዘጋጀት እንደሚበጃቸውና ሠርቶ ለመኖር ያላቸው ቁርጠኝነት ከተረጋገጠ  የመጡበት ክልል፣ ወረዳና ቀበሌ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነቱን ለመወጣት መዘጋጀቱን ማሳወቁን ገልጸዋል፡፡

አቶ የማነ ወ/ማሪያም የኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን  ግብረሰናይ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር  በበኩላቸው፣ በሀገራችን ከ200,000 ያላነሱ በልመና ተግባር ላይ የተሠማሩ ወገኖች እንዳሉ በጥናት የተደረሰበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ከነዚህ መካከል 28,000 ያህሉ መልሶ በማቋቋምና እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን መርዳት የሚችሉ አምራች ኃይል ማድረግ እንደተቻለ ገለጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 15,000 ሕፃናትና ወጣቶች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ መደረጉን አብራርተው፤ በዕለቱ በውይይቱ ላይ የተገኙትንና በቀጣይም በተቻለ መጠን በልመና የሚተዳደሩ ወገኖች ሁሉ ወደ መጡበት ቀያቸው ተመልሰው ሠርተው ራሳቸውን የሚችሉ የኢትዮጵያዊነት ኩራት የተላበሱ ዜጎች መሆን

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና የእስልምና ሐይማኖት አባቶች በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፣ ልመና በየትኛውም ሐይማኖት የማይደገፍ በመሆኑ እነዚህ ወገኖች ፈጥነው ከዚህ ተግባር መውጣት እንደሚገባቸው ጠቁመዋል፡፡ በሌላ በኩል እነዚሁ ወገኖች የመጡባቸው ክልሎች፣ አስተዳዳሪዎችና ሌሎች ባለሥልጣናትም በልመና የተሠማሩ ሰዎች ወደ ትውልድ ቀያቸው እንዲመለሱና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ለማስቻል በመንግሥት በኩል ቁርጠኛ አቋም እንደተያዘ ገልጸዋል፡፡ በቀጣይም እነዚህኑ ወገኖች ለማወያየትና ለችግሮቻቸው መፍትሔ ለመስጠት በጋራ እየሠሩ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

በውይይቱ ላይ ቁጥራቸው ከ1000 በላይ የሆኑ በልመና ሥራ የሚተዳደሩ ወገኖች እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ተሳታፊ ሆነዋል❁



*ከውይይቱ ተሳታፊ ለምኖ አዳሪዎች በከፊል*

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

# የሠራተኛውን የሙያ ደህንነትና ጤንነት የሚጠብቅ ድርጅት ለስኬት እንደሚበቃ ተገለፀ

በፌደራል የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ማስጠበቂያ ዳይሬክቶሬት በሙያ ደህንነትና ጤንነት መርሆዎችና በማህበራዊ ምክክር ስልቶች ዙሪያ ያዘጋጀው ስልጠና ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በዳይሬክቶሬቱ የስብሰባ አዳራሽ ተከፍቷል፡፡ ሥልጠናውን በንግግር የከፈቱት ክብርት ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ በኢንዱስትሪ ውስጥ የሠራተኛውን የሙያ ደህንነትና ጤንነት የሚጠብቅ ድርጅት ለስኬት እንደሚበቃ ገልፀዋል፡፡



ክብርት ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ

አያይዘውም በሥራ ቦታ ከሰው በላይ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ እንደሌለ ገልፀው ምርታማነት፣ ትርፋማነት፣ የገበያ ተወዳዳሪነት፣ የ

ሊመጣ የሚችለው የሠራተኛውን የሙያ ጤንነት ከመጠበቅና የሥራ ላይ ደህንነትን ከማረጋገጥ አንስቶ በሚከናወን የጋራ ጥረት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በኢንዱስትሪ ውስጥ የሠራተኛው የሙያ ደህንነትና ጤንነት የበለጠ እንዲጠበቅ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይ ጥረት እያደረገ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታዋ አስረድተው፡፡ ይኸኛውም ስልጠና የዚሁ አካል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ሥልጠናውን ከፋፋ ምግብ አክሲዮን እና ከኢትዮጵያ ኘላስቲክ አክሲዮን ማህበር የተውጣጡ የማኔጅመንት፣ የሠራተኛ ማህበር አመራርና የሴፍቲ ኮሚቴ አባላት የተሳተፉ ሲሆን ለ3 ተከታታይ ቀናት ተካሂዷል፡፡



የስልጠናው ተሳታፊዎች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

# የአካል ጉዳተኞች የሥራ ሥምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 የማስተዋወቅ አውደ ጥናት ተካሄደ

በፌደራል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማኅበራዊ ደኅንነት ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬትና የዓለም ሥራ ድርጅት በጋራ የአካል ጉዳተኞች የሥራ ሥምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 የማስተዋወቅ አውደ ጥናት ከነሐሴ 14-15/2001 በይርጋዓለም ከተማ ፋራ የስብሰባ ማዕከል ተካሂዷል፡፡



*አቶ ተስፋዬ ኪ/ማርያም*

አውደ ጥናቱን በንግግር የከፈቱት አቶ ተስፋዬ ኪ/ማሪያም የደቡብ ክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ኃላፊ አካል ጉዳተኞች በአገራችን 7 ሚሊዮን እንደሚደርሱ የዓለም ጤና ድርጅትን መረጃ ዋቢ አድርገው ተናግረዋል፡፡ አያይዘውም አካል ጉዳተኞች በቂ ትኩረትና ጥበቃ ስላልተደረገላቸው ለተለያዩ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መጋለጣቸውንና ከዚህም በላይ በትምህርት፣ ሥልጠናና ሥራ ሥምሪት ረገድ አድልዎ እንደተደረገባቸው ጠቁመዋው በዚህም ምክንያት መንግሥት አስከፊ የሆነውን የአካል ጉዳተኞችን ችግር ለመቅረፍ በየጊዜው የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን እንዳወጣ ተናግረው ሁሉም ባለድርሻ አካላት አዋጁን ለመተግበር ግዴታ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ከዓለም ሥራ ድርጅት፣ ቴሻየር ሆም፣ ከክልልና ዞን ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ከፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ እና የተለያዩ የፍትሕ አካላት የተሳተፉበት የሁለት ተከታታይ ቀናት አውደ ጥናት ተካሂዷል◆

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

# ወደ ተለያዩ የአረብ ሀገራት ለሥራ ፍለጋ በሚወጡ ዜጎች ዙሪያ ማብራሪያ ተሰጠ

በአሁኑ ወቅት ለሥራ ፍለጋ ወደ ተለያዩ የአረብ ሀገራት በሚወጡ ኢትዮጵያውያን ዙሪያ የፌደራል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነሐሴ 8 ቀን 2001 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ማብራሪያ ሰጥተዋል።



አቶ ካሣሁን ጐፌ

ማብራሪያውን የሰጡት **አቶ ካሣሁን ጎፌ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር** ሲሆኑ፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የዜጎችን ህገመንግስታዊ የመዘዋወር መብት መሠረት አድርጐ መብትና ደህንነታቸው ተጠብቆ በውጭ ሀገር በሥራ ሊሠማሩ

ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር 104/90 አውጥቶ በሥራ ላይ እንዲውል ያደረገ በመሆኑ፤ ዜጐች ወደ ውጪ በሚወጡበት ጊዜ ሕጋዊ የሆነ የሥራ ውል ከአሠሪዎቻቸው ጋር መፈራረማቸውንና መመዝገባቸውን የያዙት የቪዛ ዓይነትና ሕጋዊነት፣ የሕይወትና የአካል ጉዳት ኢንሹራንስ መያዛቸውን የሚያረጋግጥና እንዲሁም በሚሄዱበት አገር በሚገኘው ኤምባሲ መረጃቸው በትክክል እንዲመዘገብ የሚያደርግ አሰራር መዘርጋቱን አብራርተዋል። ዜጐች በሥራ ምክንያት ወደ ውጭ አገር ከመሄዳቸው በፊት በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሙያዎች የቅድመ ጉዞ ገለፃ (Pre-departure Orientation) ማለትም ስለሚሄዱበት አገር ባሕል፣ ስለ ሥራ ውል፣ ስልጠና፣ ወደ ውጭ አገር ሲሄዱ የሚያጋጥማቸው በጎና መጥፎ ነገሮች፣ ከአሠሪዎቻቸው ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንደሚከናወኑ ተናግረዋል። በሕጋዊ መንገድ ለሥራ ፍለጋ የሚወጡ ዜጐች ሕጋዊ፣ የሥራ ውልና የሥራ ቪዛ የሚይዙ ሲሆን፣ መረጃቸውም በተቀባይ አገር የኢትዮጵያ ኤንባሲ እንደሚመዘገብና አሠሪውም በአካል ወደ ኤምባሲ በመሄድ ውሉን የሚፈጽም መሆኑን ጠቅሰው ነገር ግን በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ የሚሄዱት ሕጋዊ የሥራ ውል የሌላቸውና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የተለያዩ ቪዛዎችን ማለትም Free Visa, Tourist Visa, Business Visa የሚጠቀሙ በመሆናቸውና ቪዛዎቹ እስከ ሁለት ወር ጊዜ ብቻ የሚያገለግሉ በመሆናቸው በባዕድ ሀገር ለከፍተኛ መንገላታትና ስቃይ እንደሚዳረጉ አብራርተዋል፡፡ ከዚህ ሌላም እነዚህ በሕገወጥ መንገድ የሚወጡ ዜጎች መረጃቸው በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደማይመዘገብና እንደማይያዝ እንዲሁም አድራሻቸውም የማይታወቅ በመሆኑ ክትትል ለማድረግ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሣ የላካቸው ደላላ እንኳን ደብዛውን ስለሚያጠፋ ለመከሰስና መብታቸውን ለማስከበር አስቸጋሪ እንደሆነ ዳይሬክተሩ አብራርተዋል፡፡



*አቶ ግርማ ሽለመ*

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሕትመት ውጤቶች ዝግጅት ባለሙያ የሆኑት አቶ ግርማ ሽለመ በበኩላቸው በሕገወጥ ደላሎች አማካይነት ተገፋፍተው ነገን በተስፋ ሰንቀው ወደ ተለያዩ የአረብ አገሮች የሚጓዙ ዜጎች ለተለያዩ ስቃይና እንግልት፣ መብት መጣስ መዳረጋቸው የተለመደ ትዕይንት መሆኑን ጠቁመው በአሁኑ ሰዓት በየወሩ ከ2000-3000 ዜጎቻችን ወደ ተለያዩ የአረብ አገራት በሕጋዊ መንገድ እንደሚጓዙ አብራርተዋል፡፡በሕገወጥ መንገድ የሚወጡትን ግን መረጃቸው ስለማይያዝና ስለማይመዘገብ ቁጥራቸውን ማወቅ አስቸጋሪ እንደሆነ ጠቁመው፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የዜጎችን መብትና ደህንነት፣ ክብርና ጥቅም ከማስጠበቅ ረገድ ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ መሆኑንና ሥራ ፈላጊዎችም ወደ ሥራ ሥምሪት ከመግባታቸው አስቀድሞ አስፈላጊውን መረጃ አግኝተው እንዲዘጋጁ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

## ከግብ እንደርሳለን

*የመሥሪያ ቤታችን ጥናት ተጀምሮ*
**አሮጌው አሠራር በአዲስ ተቀይሮ**
**የሌሎች ልምዶችም አንድ ላይ ተዳምሮ**
**ጠንክሮ ለመውጣት ተይዞል ቀጠሮ!**
**ለሁሉም ተሰጥቶ የየሥራ ድርሻ**
**በውል ተለይቶ መነሻ መድረሻ**
**ውጤት ይጠበቃል እስከ መጨረሻ!**
**እቅድና ግብን ከስኬት ለማድረስ**
**ለመሄድ ወደፊት ጀምሯል መገስገስ!**
**የቃል ኪዳን ሠነድ ሁሉም ተፈራርሞ**
**ከግብ ለመድረስ በተጠንቀቅ ቆሞ**
**በትጋት ጀምሯል አስቦና አልሞ!**
**...ቱዟችን!!**

*በሕዝብ ግንኙነትና*

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

# በረቂቅ ደንብ ላይ የመከረ ዓውደ ጥናት ተካሄደ

በፌደራል ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ማስጠበቂያ ዳይሬክቶሬት የኃይማኖትና የበጐ አድራጎት ድርጅቶች በሚመሰርቱት የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ባዘጋጀው ረቂቅ ደንብ ላይ የመከረ ዓውደ ጥናት ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስብሰባ አዳራሽ ተካሄደ፡፡



*ክብርት ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ*

የምክክር ዓውደ ጥናቱን በንግግር የከፈቱት ክብርት ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ዛሬ በሀገራችን የተለያዩ የኃይማኖት ተቋማት ዕምነትን በነፃነትና በእኩልነት ከማራመድ ጐን ለጐን ተከታዩቻቸውን በሠላምና በልማት አገራዊ አጀንዳ ውስጥ በማሳተፍ ትርጉም ያለው ድርሻ እያበረከቱ መገኘታቸው የሚያስመሰግናቸው ተግባር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም የበጐ አድራጎት [illegible] ክፍሎች ከሚሰጡት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት በተጓዳኝ ልማትን ለማፋጠንና ከድህነት ለመላቀቅ በሚደረገው የጋራ ጥረት ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ተግባር እያካናወኑ መገኘታቸው ማህበራዊ ኃላፊነትን የመወጣት መገለጫ ነው ብለዋል፡፡ ተቋማቱ ተልዕኳቸውን ለመወጣት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከሚያስፈልጋቸው የሰው ኃይል አኳያ በቅጥር ላይ የሚመሰረት የሥራ ግንኙነት መፈጠሩ ስለማይቀር ይህ የሥራ ግንኙነት በደንብ እየተመራ የጋራ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ረቂቁ መዘጋጀቱን አስረድተዋል፡፡

በዓውደ ጥናቱ ላይ ከተለያዩ የኃይማኖት ተቋማት፣ ከበጐ አድራጎት ድርጅቶች፣ ከአሠሪና ሠራተኛ አካላት፣ ከመንግስት አስፈፃሚ ተቋማት የተውጣጡ ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን ረቂቁ ደንብ ሆኖ በሚወጣበት ጊዜ በባለድርሻ አካላት ዘንድ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የሚያስችል የማዳበሪያ ምክክር አካሂደዋል፡፡



***የዓውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በከፊል***

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

# ይድረስ ለወ/ሮ ፌቨን

## ግስላው ከሰንቦ

አንዳንድ ጊዜ *"ይገርማል"* እያሉ አግራሞትን ከመግለፅ ያለፈ መናገር የማይቻልበት ነገር ያጋጥማል፡፡ እኔም ይገርማል በማለት ብቻ ያሳለፍኩት ጉዳይ ስፍር ቁጥር የለውም፡፡ አሁን ግን ወንዶችን ሰብስቦ ባልትና ማሰልጠን ድህነትን ይቀንሳል በማለት አንቺ ያነሳሽው ርዕሰ ነገር በዝምታ የሚታለፍ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ይልቁንም በጊዜ እንዲታረም አፀፌታ የሚያሻው በመሆኑ ትክክል የመሰለኝን ለማለት ሙያው ባይኖረኝም ብዕር አንስቻለሁ፡፡

ወንዶችን ባልትና አሰለጥናለሁ ብለሽ የተነሳሽበት ነገር ሠልጥነው ዓለምን ያሰለጠኑ ስልጡን ወንዶችን ማህበራዊ ደረጃ ወደ ታች ከማውረድ ያለፈ ግብ ይኖረዋል ተብሎ በወንዶች በኩል አይታሰብም፡፡ በዚህ ረገድ ያለረድፉ ገብቶ የፌቨንን ሃሣብ እጋራለሁ የሚል ወንድ ከተነሳ ደግሞ ሴታሴትነቱን ከሚነግረን በቀር እኛ ወንዶች እሱን አንከተልም፡፡

ምነው ፌቨን?! የጥንት የመሰረቱን ባህልና ወግ አክብረውና አደብ ገዝተው የተቀመጡ ጨዋ ሚስቶችን ልብ በሚያሸፍት ዓይነት በባሎች ላይ ብዕር መምዘዝ በሚስቶችም ሆነ በባሎች ዘንድ እንደ ደግ ሥራ ይቆጠርልኛል ብለሽ ከሆነ ግምትሽ ፋርሽ መሆኑን ቢያንስ ከኔ መልስ አሰጣጥ ልትረጂው ይገባል፡፡ በየራሳችን ጣርያ ስር ያለውን የአኗኗር ዘይቤ አደባባይ እያወጣን በመለፈፍ የሚገኘው ማህበራዊ ፋይዳ ምን እንደሆነ በግሌ አይገባኝም፡፡ ስለሆነም *"ድህነትን ለመቀነስ ወንዶችን ማሰልጠን"* በሚል ርዕስ ለንባብ ባበቃሽው ጽሑፍ የተነሳ ሌሎችም ሃሳቡን እየደገሙ መውቀጥ ከመጀመራቸው አስቀድሞ በይፋ ይቅርታ ልትጠይቂ ይገባል እላለሁ፡፡

***ፌቨን***- ወንዶችን ባልትና የማሰልጠን ዕቅድሽ ማሰልጠኛ ማዕከል እስከ ማቋቋም የደረሰ ርቀት ከመጓዙ አስቀድሞ ወንዶች እንደ ባለድርሻ ተቆጥረው ቢመክሩበት ኖሮ ሃሳቡ ማጀት ውስጥ ተዳፍኖ ይቀርና አነጋጋሪነት አይኖረውም ነበር፡፡ እዚህ ላይ ቢያንስ፡- *"ሴት ያውቃል **በወንድ ያልቃል**"* የሚለውን ዕድሜ ጠገብ አገራዊ ብሒል ማሰብ ነበረብሽ፡፡

አይ ፌቨን! ምድረ ወንድ ባልትና ሰልጥኖ ሲያበቃ የቤት ሠራተኛ አያስፈልግም፤ የዚህ ድምር ውጤት ደግሞ ድህነትን ይቀንሳል የሚለው የተወላገደ ሃሳብሽ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ሲገርመኝ ይኖራል፡፡ በሌላ በኩል እንዲህ ዓይነቱ የነገር አተላለም በየጣርያው ሥር በሰላም እየሰሩ በሚኖሩ የቤት ሠራተኞች ላይ የመፈናቀል አደጋ ለማስከተል የታለመ ይመስላል፡፡ እንዲያውም ጽሑፉን ያነበበች አንዲት የቤት ሠራተኛ ሥጋቷን በግልፅ አውርታልኛለች፡፡ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ የቤት ሠራተኞች የሥራ ዋስትና አደጋ ላይ ከወደቀ ደግሞ ድህነት ይባባሳል እንጂ እንዴት እንደሚቀንስ የአንቺ ጸሑፍ የማሳየት አቅም የለውም፡፡

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እናስ?! እነዚህ ዜጐች የት ይውደቁ ብለሽ ነው የነሱን ቦታ የየቤቱ አባወራ ተክቶ ማድቤቱን ሊረከብ ይገባል የሚል ክርክር ያነሳሽው?! የመረጥሽው ርዕስ ጉዳይ የባልትና ማሰልጠኛ ከፍቻለሁ የምትይውን ተቋም የማስታወቂያ ሂሳብ በማይከፈልበት ዘወርዋራ ብልጠት ለማስተዋወቅ ካልሆነ በስተቀር ቁም ነገር የለውም፡፡ አይ ምነው እቴ! ማስታወቂያም እኮ የረባ ጉዳይ ከሌለበት ነገሬ የሚለው አይኖርም፡፡

ፌቨን ትልቁ ችግርሽ ወንድ ለማድ ቤት ሥራ እንዳልተፈጠረ የመረዳትና አምኖ የመቀበል ጉዳይ መሆኑን ጹሑፍሽ ያስረዳል፡፡ ቀሚስ ማጥለቅ ያስፈለገው እኮ ለማድቤት ሥራ እንዲያመች እንጂ ውበትን ለማሳመር ብቻ አይደለም፡፡ ሱሪ ደግሞ ልብስ ብቻ ሳይሆን የወንድነት መገለጫ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሱሪ ታጣቂው በያደባባዩ በኰራ ግርማ ሞገስ ቢንጐራደድ ያምርበታል፡፡ ማድቤትማ ለወንድ ልጅ ያለሥፍራው መገኘት ይሆናል፡፡ እርግጥ ነው ሱሪ የመልበሱ ነገር ዛሬ ጊዜ የጋራ ቢሆንም ወንዶች ቀሚስ በሚሸጥበት ቡቲክ ገብተው ሲለኩ አልታየም፡፡ እናም ወንድ ደጅ ደጁን መንጐራደድ እንጂ ኩሽና ገብቶ ሽንኩርት መቀርደድ የወግ አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ በሴትና በወንድ መካከል ማህበራዊ ድንበር የተበጀለት የሥራ ክፍፍል መኖሩንና ፀንቶ መቆየቱን ስለሚያሳይ ደንብ የማፍረስ ሙከራሽ ለደንብ በሚቆረቆሩ ወንዶችና ሴቶች ፉርሽ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ በዚህ ረገድ በሴቶችም ሆነ በወንዶች በኩል ሃሳብሽን የመዋጋቱ የጋራ ጥረት እንደሚቀጥል ይገመታል፡፡

***ፌቨን፡-*** ወንድ ባልትና እየሰለጠነ የወጥ ቤትን ሥራ የእኩሌታ ያድርገው የምትይው ነገር ከኔ ባለቤት ጨዋ አመለካከት ጋር እንደማይገጥም ለማሳየት አንድ ነገር ልጥቀስልሽ፡፡

አንድ ጊዜ ውዷ ባለቤቴ ወጥ ቤት ውስጥ የበግ ሥጋ ለመጥበስ ስትዘጋጅ ጐራ አልኩና የዛሬውን እኔ ልጥበስ አልኳት እንደዘበት፡ ፡ . ብለህ ብለህ የሰፈር ቡና መጠጫ አድርገኸኝ!! የሷ ባል ሴታ ሴት ስለሆነ ወጥ ቤት እየገባ በማማሳያ ይቀምሳል እያሉ በሹሙጥ ይገሽልጡኛል!...መጥበሱ ይቅርና ኩሽና መግባትህም ነውር ስለሆነ ድምፅህን አጥፍተህ ውጣ!.... እያለች ያባረረችኝ ትዝ ይለኛል፡፡ ይህ አድራጐቷ ወግና ልማድ ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያስችል የጨዋ ሴት ተግባር ስለሆነ ልትመሰገን ይገባል፡፡

ይሁንናም የተከበሩ ወንዶች ባርኔጣና ካፖርታቸውን አውልቀው ያለወጉ ማድቤት መግባታቸው ድህነትን ይቀንሳል ያልሽው ነገር እንዳልተዋጠልኝ የምነግርሽ ከልቤ ነው፡፡ ጽሑፍሽን ያነበቡ ሴቶችና ወንዶች ፌቬን የማይሆን ጉዳይ አመጣች እያሉ ነገርሽን ሲያጣጥሉት መስማቴም ሃሳብሽን ለመሞገት አነሳስቶኛል፡፡ ስለመሰልጠን ካነሳሽ አይቀር ደግሞ ሴቱም ወንዱም እኩል ሊሰለጥን ይገባል የሚል መነሻ ብትይዥ እንኳ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ ሴት ስለተሆነ ብቻ የማድቤት ሥራ ይቀላጠፋል ማለት የተሳሳተ ነገር ነው፡፡ እኛ ወንዶች የሚጥምና የማይጥም መሰናዶ የሚያጋጥመን በሴቱ መሃል የባልትና መበላለጥ በመኖሩ የተነሳ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ከባልትና ጋር የማይተዋወቁና በዚህ አግባብ ከወንዶች ጋር እኩልነታቸውን ያረጋገጡ አያሌ ሴቶች መኖራቸው እየታወቀ ወንዶችን ብቻ ነጥሎ የማሰልጠን ሃሳብ እነዚህን ሴቶች እንዲበለጡ ማድረግ ይሆናል፡፡

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!



ሌላው የገረመኝ ነገር የቤት ውስጥ ዓመሌ የአንቺው ባል ዓይነት ሆኖ የመገኘቱ አጋጣሚ ነው፡፡ ከዚሁ የተነሳ የነገርሽ ቀስት ሁሉ እኔም ላይ ያነጣጠረ ስለመሰለኝ ዝም ማለት አልቻልኩም፡፡ ልዩነታችን የኔ ባለቤት ኑሯችንን የሚደጉም ገቢ በማምጣት በኩል የለችበትም፡፡ እኔ ሠርቼ የማመጣውን አብቃቅተን እየኖርን ነው፡፡ ይኸ የሆነው ደግሞ ሥራ ጠፍቶ ሳይሆን የምርጫ ጉዳይ ነው፡፡ ሴት ልጅ ከቤት ከወጣች ጣጣው ብዙ ነው፡፡ እኔማ እንኳን ውጭ እንድትውል መፍቀዱ ይቅርና ተባዕት እንግዳ ከቤታችን ሲመጣ እሷ ወደ ጓዳ ሆና በሠራተኛችን እንዲስተናገድ ማድረግ የቤታችን ደንብ የሆነው ከጋብቻችን አንስቶ ነው፡፡ አደባባይ መውጣት ከተጀመረ የአይናፋርነት ፀጋ እየተገፈፈ በሥፍራው ዓይናውጣነት መተካቱ እንደማይቀር ከወዲሁ ስለሚታየኝ ከቤት እንድትውል ማድረጌ ጠንቃቃነት ነው፡፡

አይ ፊቨን! ስለትንኮሳ ያነሳሽው ጉዳይ ደግሞ የሚያስተዛዝብ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ለመሆኑ ትንኮሳ ምንድነው? የትንኮሳን ትርጓሜ ለጊዜው በመተው የአተነካኮስን ጠባይ ብንመለከት እንኳ ነገሩ ወዲያና ወዲህ ሆኖ መገኘቱ አይቀርም፡፡ በአንደበት ከሚገለፀው ይልቅ በድርጊት የሚሆነው እንደሚብስ ልቦናሽ እያወቀ ወንዶችን ብቻ በተንኳሽነት መፈረጅሽ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

የትንኮሳ ነገር ከጥንት እስከዛሬ በእናንተ አይብስም?! ዓይናችሁ፣ ፀጉራችሁ፣ ዳሌያችሁ፣ ልብሳችሁ፣ ሳቃችሁ፣ አረማመዳችሁ፣ ሽቷችሁ እራሱ ተፈጥሯችሁና ነገረ ሥራችሁ ሁላ ከትንኮሳ የፀዳ ስለመሆኑ ማነው ምስክሩ?! ታዲያ ከምን የተነሳ ነው በዚህ ጉዳይ ላይ ወንዶችን ብቻ ነጥሎ ተወቃሽ ማድረግ የሚቻለው?! ለነገሩ አንቺ ነጥቡን ስላነሳሽው እንጂ በግሌ በትንኮሳው ተርታ የሌለሁ ጨዋ ነኝ፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ ተሳክቶልኝ ባለቤቴን ለማግኘት አብቅቶኛል፡፡ ያንጊዜም ቢሆን እሷ ልትሆን ትችላለች የተነኮሰችኝ፡፡ በሌላ በኩል ካልተተነኮሱ ወንድን እንደወኔ ቢስ የሚቆጥሩ ሴቶች መኖራቸውንም መመልከት ሚዛናዊ ያደርጋል፡፡ በዚህ አግባብ ሴቶችና ወንዶች ሲተነኮኮሱ መዋላቸው ማብቂያ የሚኖረው አይመስለኝም፡፡ በዚህ አግባብ ትንኮሳ መስተጋብራዊ እንጂ ከአንድ ወገን ብቻ የሚነሳ አድርጐ መመልከት ያስቸግራል፡፡

የመልስ ጽሑፌን ከማብቃቴ በፊት ማንሳት የምፈልገው ነገር አለ፡፡ ወንዶችን ባልትና ካላሰለጠንኩ ሞቼ እገኛለሁ ማለትሽ ዋናው መነጋገሪያችን ቢሆንም የአንቺም የባልትና ብቃት አጠራጣሪ ሆኖብኛል፡፡ እንዴት ያልሽ እንደሆነ ባለቤትሽ “.ቁርስ አልደረሰም ወይ?...ቡና አላፈላሽም እንዴ?......” እያለ በመጐትጐት እንጂ በትጋትና በቅልጥፍና ሠርተሽ ማቅረብ እንደማይሆንልሽ ጽሑፍሽ ፍንጭ አሳይቷል፡፡

የኔዋ ግን “ግስላ! ግስል! ግስሎ! ግስሌ! ተነስ ቁርስ ደርሷል” .” እያለች ከመኝታዬ የምትቀሰቅስበትን የባልትና ብቃት በንፅፅር ስመለከተው የአንቺ ባለቤት በሚስት እንክብካቤ በኩል የተጐዳ ይመስለኛል፡፡ ዕድሉና ምርጫው ስለሆነ ይቻለው እንግዲህ” ”

በመጨረሻም ፊቨንን ጨምሮ የመልስ መልስ እሰጣለሁ ብላ የምትነሳ ብትኖር ወይም የሚነሳ ቢኖር እኔ ግስላው የማልፈራ መሆኔን

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

# ጠበኪያ ጊዜ



ሶደሬ ውስጥ መኪና ላይ
ስትሳፈር ለታየቸው
ጦጣ

መሄዴ ነው በቃ ልግባ ከተማ
ድንገት ተሳፍሬ ቤተሰብ ሳይሰማ!
እንኳ ንስ ቤተሰብ ሹፌሩም አላየኝ
ድንገት ከተነቃ ክፊይኝ እንዳይለኝ!
በኪሴ አንዳች የለ ገንዘብ ቤሳቤስቲ
ከየት አመጣለሁ ክፊይ ቢለኝ እስቲ!
ታዲያ ምን ይሻላል ወይም ህግ አልወጣ
በነፃ እንዲሳፈር እንዳይከፍል ጦጣ!
ጫካ የቀራችሁ እናትና አባቴ
እህት ወንድሞቼ አክስትና አጐቴ!
እንዳትሸበሩ የት ገባች ብላችሁ
ወደ አዲስ አበባ ሄጃለሁ ልጃችሁ!

ቢሆንም፡

**የሹፌሩ አነዳድ ካልሆነልኝ መልካም**
**እያንገጫገጨ ካበዛብኝ ድካም**
**በደህንነቴ ላይ ሥጋት ከፈጠረ**
**ደጋው ከበረደኝ እያንጠረጠረ!**
**ድንገት ከተጣላኝ የነዳጁ ሽታ**
**እንዳልተስማማው ሰው ጠጥቶ መሸታ**
**መልካም ካልሆነልኝ ካልተመቸኝ ኑሮ**
**ብይ ከተባልኩኝ ዘወትር በሽሮ!**
**ሙዝና ብርቱካን ካልሆነ ቀለቤ**
**መመለሴ አይቀርም ወደቤተሰቤ!!**
**ደግሞ ዛፍ ከሌለ ከነፍራፍሬው**
**ጓደኛ ከጠፋ የምኖር አብሬው!**
**በህልሜ ከመጣ ሶደሬ ውበቱ**
**ጭንቀት ከሆነብኝ ቤተሰብ ናፍቆቱ**

ከባሳዝን ደርቤ
ከባሳዝን ደርቤ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!